# የኢየሱስ ክርስቶስን በዓለ ሆሣዕና እና
# በዓለ ትንሣኤ፡ ክርስቲያኑ ዓለም፡
# በያመቱ፡ እያከበረ ያለው፡
# እንዴት ነው? በእውነት ነውን?

---

ለሰው ልጆች መልካም ሕይወት፡
ጠንቅ የኾነው ጥያቄ፡
አጥጋቢዉን የመፍትሔ መልስ:
ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ አግኝቷል።

---

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡
ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ፡
እስካረገባት ዕለት ድረስ፡
አርባ ቀን ሙሉ፡ ምን ሲያደርግ ቆየ?

---

ለቅዱሳንና ለቅዱሳት አማኞቹ ሓዋርያት
እየተገለጠላቸው፡
## ስለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት
ሲነግራቸውና ሲያስተምራቸው ነዋ!

---

የቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት
ልጆች፡ እነዚህንና ሌሎቹን በዓላት የሚያከብሩበት:
ትክክለኛው የሃይማኖትና የምግባር ሥርዓት።

---

የምሥራች! ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ፡ በቅዱሳን ነብያቱ ቃል ሲነገር የቆየውን ማንነቱን፡ ለዓለሙ፡ በይፋ ለማስታወቅ፡ እንደምድራውያን ነገሥታት፡ በፈረስና በሠረገላ ሳይሆን፡ በአህያ ውርንጭላ ላይ ተቀምጦ፡ ወደኢየሩሳሌም ከገባበት፡ ከዚያች፡ የዛሬ ኹለት ሺህ ዐሥራ አምስተኛው ዓመት የሆሣዕና ዕለት ጀምሮ፡ እስከመጪዋ የሆሣዕና፡ የንጉሥነቱ በዓል፥ ቀጥሎ ደግሞ፡ በሚመጣው ሳምንት እስከምንዘክረው፡ የትንሣኤው በዓል ድረስ ያሉትን ዓመታውያን መታሰቢያዎች፡ በእግዚአብሔር እውነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኮት፡ በትክክለኛ መልኩና ይዘቱ ያከበረና የሚያከብር ማነው?

በትክክለኛ መልኩና ይዘቱ ያከበሩና የሚያከብሩ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ባለቤትና የቅዱሱ ኪዳን ባለአደራ የኾነችው ኢትዮጵያ፡ የእርሷ ልጆች የኾኑት፡ የቀደሙት ኪዳናውያንና ኪዳናውያት በመኾናቸው፥ አዎን! እኛም፡ የዛሬዎቹ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት በመኾናችን፡ እጅግ ደስ ይበለን!

ለምንና እንዴት ይህ ኾነ? ትክክለኛውንና እውነተኛውን ምክንያት፡ በመንፈሳዊ ማስተዋልና በሃይማኖታዊ ትኩረት ኾነን፡ ከዚህ በታች የሠፈረውን ማብራሪያ እንመልከተው!

በእነዚያ፡ በብሉዩ ኪዳን ዘመን በተነሡት፡ ቅዱሳን ነቢያት አንደበት፡ **"እስመ ለእግዚአብሔር መንግሥት!...እግዚአብሔርሰ፡ ንጉሥ ውእቱ እምቅድመ ዓለም፤ ...ይነብር እግዚአብሔር፡ ወይነግሥ ለዓለም፤"**

ማለትም፡ **"መንግሥት የእግዚአብሔር ናት! ...እግዚአብሔርማ፡ ከዓለም መፈጠር አስቀድሞ፡ ንጉሥ ነው! ...እግዚአብሔር፡ ለዘለዓለምም፡ ነግሦ ይኖራል!"** የተባለለት ፈጣሪ፡ በመጨረሻው ዘመን፡ ከድንግል ማርያም ተወልዶና በሰውነት ተገልጾ፥ በቤዛነቱም፡ የዲያብሎስን፥ የኃጢአትንና የሞትን ጠንቀኛ ኃይላት አስወግዶ፡ መንግሥቱ፡ በምድር ላይ ተመልሳ እንድትሰፈን አደረገ።

በዚያን ጊዜም፡ እርሱ፡ "ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ!" ተብሎ፡ ንጉሥነቱን፥ **"ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር!"** የተባለችውን የቅድስት እናቱንም፡ ንግሥትነት አረጋግጦ ዐተመ። (መዝ. ፳፩፥፳፰። ፳፰፲። ፸፫፥፲፪። ፷፯፥፴፩። ራእ. ፲፩፥፲፭።)

በአዲሱ ኪዳኑም ዘመን መግቢያ ላይ፡ የነቢያት መጨረሻና የሐዋርያት መጀመሪያ ሆኖ የተነሣው፡ መጥመቁ ዮሐንስ፡ **"ወበውእቱ መዋዕል፡ በጽሐ ዮሐንስ መጥምቅ፡ እንዘ ይሰብክ፡ በገዳመ ይሁዳ ዘዮርዳኖስ፤ እንዘ ይብል፡ 'ነስሑ! እስመ ቀርበት መንግሥተ ሰማያት!'"**

ማለትም፡ "**በዚያን ወራት፡ መጥምቁ ዮሐንስ፡ 'የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና፡ ንስሓ ግቡ!' እያሉ፡ የዮርዳኖስ አውራጃ በምትሆን፡ በይሁዳ ምድረ በዳ እየሰበከ መጣ።"** ተብሎ እንደተጻፈው፡ መጥመቁ ዮሐንስ የምሥራቹ አዋጅ ነጋሪ ኾኖ የተላከው፥ የመጣውና የሰበከው፡ በውስጧ፡ ቤተ ክርስቲያንን ስላካተተችው፡ ስለእግዚአብሔር መንግሥት ብቻ መሆኑን፡ ጥቅሱ ያሰረዳል። (ማቴ. ፫፥ ፩-፪።)

ራሱ፡ የእግዚአብሔር ልጅ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ **"ወእምድኅረ አኀዝዎ፥ ወሞቅሕዎ ለዮሐንስ፡ መጽአ እግዚእ ኢየሱስ ገሊላ፤ ወሰበከ ወንጌለ መንግሥተ እግዚአብሔር፤ ወይቤ፡ 'በጽሐ ጊዜሁ፤ ወቀርበት መንግሥተ ሰማያት፤ ነስሑ! ወእመኑ በወንጌል!"**

ማለትም፡ **"ዮሐንስን ከያዙትና ካሠሩት በኋላ፡ ጌታችን ኢየሱስ፡ ወደገሊላ መጣ፤ የእግዚአብሔርን መንግሥት ምሥራችም ሰበከ! እንዲህ እያለ፡ 'ጊዜው ደረሰ! መንግሥተ ሰማያት ቀረበች! ስለዚህ፡ ንስሓ ግቡ! በምሥራቹም እመኑ!"** ተብሎ፡ እንደተጻፈው፡ ሰው ኾኖ፡ ወደዚህ ዓለም የመጣውና የሰበከው፡ በውስጧ፡ ቤተ ክርስቲያንን ስላካተተችው፡ ስለእግዚአብሔር መንግሥት ብቻ መኾኑን፡ ይኸኛውም ጥቅስ ያስገነዝባል። (ማር. ፩፥ ፲፬-፲፭።)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ይህንኑ የምሥራች ስብከቱን፡ **"መንግሥተ እግዚአብሔርሰ፡ ነያ ማዕከሌክሙ ይእቲ!"** ማለትም፡ **"የእግዚአብሔር መንግሥት በውስጣችሁና በመካከላችሁ ናት!"** እያለ፡ ከጥምቀቱ ጊዜ ጀምሮ፡ እስከትንሣኤው ድረስ፡ የአዋጅ ቃሉን መቀጠሉ ይታወሳል። (ሉቃ. ፲፯፥ ፳፩።)

ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላም፡ እስከዕርገቱ ድረስ፡ አርባ ቀን ሙሉ፡ ለቅዱሳን ሐዋርያቱ፡ ሲነግራቸውና ሲያስተምራቸው የቆየው፡ በውስጧ፡ ቤተ ክርስቲያንን ስላካተተችው፡ ስለዚችው መለኮታዊት መንግሥቱ ብቻ እንደነበረ፡ እንዲህ የሚለው፡ የቅዱሳቱ መጻሕፍት ቃል ያረጋግጣል፡-

"ቀዳሚ፡ ጸሓፍኩ ለከ፡ መጽሓፈ፤ አ ቴኦፊላ! በኩሉ ግብር፡ ዘአኀዘ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ይግበር፥ ወይምሀር፡ እስከዕለት፡ እንተ ባቲ ዐርገ፤ አዚዞ ለሓዋርያቲሁ፡ ለእለ ኀረዮሙ በመንፈስ ቅዱስ። እሉ እሙንቱ፡ እለ እርአዮሙ ርእሶ ሕያወ፡ እምድኅረ ሞተ፡ በተአምር ብዙኅ፤ <u>አርብዓ ዕለተ፡ እንዘ ያስተርእዮሙ፤ ወይዜንዎሙ፤ ወይነግሮሙ፡ በእንተ መንግሥተ እግዚአብሔር።"</u>

ማለትም፡ "ቴዎፍላ ሆይ! ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ሊያደርገውና ሊያስተምረው የጀመረውን ሥራ፥ በመንፈስ ቅዱስ የመረጣቸውን፡ ሓዋርያትን አዝዞ፡ እስካረገበት ቀን ድረስ ያለውን ኹሉ፡ አስቀድሜ፡ በመጽሓፍ ጻፍሁ፤ ብዙ ተአምራትን በማሳየት፡ ከሞተ በኋላ፡ ሕያው ራሱን የገለጠላቸው፥ <u>አርባ ቀን ሙሉ እየተገለጠላቸው፡ ስለእግዚአብሔር መንግሥት የነገራቸውና ያስተማራቸው፡ እነዚህ ናቸው።"</u> (የሓዋ. ፩፥ ፩-፫።)

ለምሥራቹ ስብከት ሥርጭትና መስፋፋት፡ ቀዳሚ ሓዋርያ የነበረው፡ ቅዱስ ጳውሎስም፡ የተልእኮው ዓላማና ተግባር፡ በዚህችው፡ በውስጧ፡ ቤተ ክርስቲያንን ባካተተችው፡ <u>የእግዚአብሔር መንግሥት</u> ላይ ብቻ ያተኮረ እንደነበረ፡ እንዲህ የሚለው፡ በዚሁ የቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የተመዘገበው ቃል ሲመሰክር ይገኛል።

"ወመጽኡ ኀቤሁ ብዙኃን፡ ኀበ ሀሎ የሀድር፤ <u>ወነገሮሙ፡ በእንተ መንግሥተ እግዚአብሔር</u>፤ እንዘ ያሰምዖሙ፥ ወያአምኖሙ፡ በእንተ እግዝእነ ኢየሱስ፡ እምኦሪተ ሙሴ፥ ወእምነቢያት፤ <u>እምነግህ እስከሠርክ</u>።

"ወነበረ ጳውሎስ ኀበ መካን፡ ዘተአሰበ በንዋዩ፡ ክልኤተ ዓመተ፤ ወይትቄበል ኲሎ ዘአተወ። <u>ወይጼውዖሙ ለመንግሥተ እግዚአብሔር፤ ወይሰብክ፤ ወይሜህር</u>፡ በእንተ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ፤ ወእንዘ ክሡተ ይነግር፤ ወአልቦ ዘይከልአ።"

ማለትም፡ "ብዙዎች፡ ወዳረፈበት ቤት፡ ወደእሩስ መጡ፤ እርሱም፡ ስለጌታችን ኢየሱስ፡ ከሙሴ ኦሪትና ከነቢያት እያስረዳ፥ እያስተማመነም፡ <u>ከጧት እስከማታ፡ ስለእግዚአብሔር መንግሥት ነገራቸው።</u>

**"…ጳዎሎስም፡ [በሮሜ] በገንዘቡ በተከራየው ቤት፡ ኹለት ዓመት ተቀመጠ፤ ወደእርሱ የመጣለትንም ኹሉ ይቀበል ነበር። ወደእግዚአብሔር መንግሥት ይጠራቸው፥ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስንም ነገር ይሰብክ፥ ያስተምርም ነበረ፤ በግልጥ ሲያስተምርም፡ የሚከለክለው አልነበረም።"** (የሓዋ. ፳፰፥ ፳፫፤ ፴-፴፩።)

*መቼም፡ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት፥ እነርሱም፡ እየራሳቸውን፡ 'ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ነን! [እንደኢትዮጵያ]' ፥ ወይም፡ 'ብቻው ኦርቶዶክስ ነን! [እንደግብፅና ግሪክ]'፥ የሚሉት ተቋሞች፡ "በኢየሱስ ክርስቶስ የተገለጠውን፡ የእግዚአብሔርን ፈቃድ፥ የተነገረውንም ቃል ለመፈጸም የቆምን ድርጅቶች ነን!" እንደሚሉ፡ በይፋ ይቃወቃል።*

እርግጡ ይህ ከኾነ፡ *ታድያ!* ከእነርሱ መካከል፡ ***"አንተሙሰ፡ ኅሡ መቅድመ፡ መንግሥቶ ወጽድቆ!"***

*ማለትም፡* ***"እናንተስ፡ አስቀድማችሁ፡ የእግዚአብሔርን፡ መንግሥቱንና እውነቱን ሹ!*** *ፈልጉ!" ባለው መሠረት፡ "እኔ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ነኝ! መመሪያየም፡ የእርሱ እውነት ናት!" ማለቱ ቀርቶ፡ ስለእግዚአብሔር መንግሥትና ስለእግዚአብሔር እውነት ሲሰብክና ሲያስተምር፥ ሲናገርና ሲጽፍ፥ ሲሠራና ሲያሰሥራ የሚታየው፡ የትኛው ቤተ ክርስቲያን፥ የትኛው ቤተ ክህነት ነው?*

*ኹሉም፡ የእግዚአብሔር የኾነችውን እውነት፡ በሓሰት ለውጠው፥ የእግዚአብሔር ብቻ የኾነችውን መንግሥትንም፡ ለሰይጣናውያን ሰዎች፡ አሳልፈው ሰጥተው፡ የሚሰብኩትና የሚያስተምሩት፥ የሚናገሩትና የሚጽፉት፥ የሚሠሩትና የሚያስሡሩት "ቤተ ክርስቲያን" ስለሚሉት፡ ሰው-ሠራሽ አቋማቸው ብቻ አይደለምን? አዎን! እውነታውና ትክክሉ ይህ ነው። (ሜቴ. ፮፥ ፴፫።)*

*በመላው የምድር ስፋት ላይ ተበትነውና ተከፋፍለው የሚገኙት የዓለም ሕዝቦች ኹሉ፡ "ክርስቲያኖች" የሚባሉት ጭምር፡ እነሆ፡ በባዕድ አምልኮና በሰይጣናዊ ሥርዓት የሚመራውን፡ የሰዎች መንግሥት እያቋቋሙ ሲኖሩ፤ በኢየሱስ ክርስቶስ ንጉሥነትና በድንግል ማርያም ንግሥትነት የምትመራውን፡ ይህችን ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ መንግሥታቸው አድርገው እስካኹን የኖሩት፥ አኹንም እየኖሩ ያሉት፥ ወደፊትም የሚኖሩት፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያ ልጆች ብቻ መኾናቸው፡ በእርግጥ ያስደንቃል፥ ያስደስታልም፡*

ፈጣሪ፡ እያንዳንዳችንን በመልኩ በመፍጠሩ፡ ባጎናጸፈን የእውቀት ጸጋ፡ እናንተም፡ ይህን እውነታ፡ በያላችሁበት፡ በሚበቃ እንደተገነዘባችሁት እናምናለን፤ ይሁን እንጂ፡ በዓለም ያሉ፡ የተለያየ ሃይማኖት ያላቸው ብቻ ሳይኾኑ፥ ክርስቲያኖቹ ጭምር፥ እየራሳቸውን፡ የ"እግዚአብሔር መንግሥት" ብለው በመጥራት ፈንታ፡ "ቤተ ክርስቲያን" **ወይም፡ "ቤተ ክህነት"** ብለው በመሠየማቸው፥ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደሌለችም በመቁጠር፡ ካህናቶቻቸውና ምእመኖቻቸው፡ ከሌሎች አማኞች ጋር በመቀናጀት፡ ከእግዚአብሔር ውጪ የኾነ፡ ሌላ ተጻራሪ "የሰዎች መንግሥት" እንዲያቋቁሙ በመፍቀዳቸው፡ እነሆ፡ ራሳቸው፡ የአብያተ ክርስቲያናቱ መሪዎች ሳይቀሩ፡ የዚያ የሰዎች መንግሥት ተባባሪዎች ኾነው ሲሠሩ መታየታቸው ያስገርማል።

ከኹሉ ይልቅ፡ ራሷን "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን" ብላ የምትጠራው፡ በኢትዮጵያ፡ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ቅርንጫፍ የኾነችው፡ የዛሬዋ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት፡ **በቅዱሱ ኪዳን ላይ፡ ታላቁን የክህደትና የዓመፅ፤ የአመንዝራነትም ኃጢአት፡ በይፋ በመፈጸም፡ ከኢትዮጵያ ተፃራሪዎች ጋር፡** ያለይሉኝታና ያለኀፍረት የምታካኺደው ግበረ አበርነት እጅግ **ያስተዛዝባል።** ይኸውም፡ ከላይ በተጠቀሰው የእግዚአብሔር ቃለ መሠረት፡ ለሰባት ሺህ መቶ ዐሥራ አምስት ዓመታት ጸንቶና ተጠብቆ የኖረውን፡ የኢትዮጵያን መለኮታዊ ሥርዓተ መንግሥት ለማፍረስ፡ "እግዚአብሔር የለም!" የሚለውን ሰይጣናዊ መፈክር አንግቦና በይፋ አውጆ፡ በተግባር ላይ ከዋለው፡ ከደርግ አገዛዝ ጀምሮ፡ ይኸው እስከዛሬ ድረስ፡ ከየዘመኑ ቤተ ሕዝብና ቤተ ምልክና ጋር ተባባሪ **ኾና እየፈጸመች ያለው የጥፋት ሥራ ነው።**

በዚህ አንጻር፡ የቅርቦቹ ቅዱሳን ኢትዮጵያውያንና ቅዱሳት ኢትዮጵያውያት ሰማዕታት፥ ከነርሱም መካከል ስማቸው ጎልቶ የሚታወቀው፡ እነቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ሚካኤል፡ **"ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በቀር፡ ሌላ የምናውቀው፥ የምንቀበለውም፡ ባዕድ መንግሥት ፈጽሞ የለም!"** በማለታቸው፡ በካቶሊካዊው ፋሽስት የኢጣልያን የግፍ ጦር መሣሪያ የተሠየፉበት ዜና መዋዕል፡ እዚህ ላይ፡ ለዝክረ ነገር ብቻ ሳይኾን፡ ለምስክርነት ጭምር፡ ማስረጃ ኾኖ ሊቀርብ ይገባዋል።

ታድያ! ከ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. ወዲህ የኾነውን፡ የየቀኑን ድርጊት ትተን፡ እዚህ ላይ በተያያዝነው ርእስ ብቻ እንወሰንና፡ በያመቱ በሚከበረው የሆሣዕና እና የትንሣኤ በዓላት ላይ የሚጸለየው ጸሎት፥ የሚዘመረው ዝማሬ፥ የሚካኼደው ማኅሌት፥ የሚታጠነው

ማዕጠንት፥ የሚቀደሰው ቅዳሴና የሚቀርበው መሥዋዕት ለማን ነው? ***“መንግሥቱ ዘለዓለም! ወምኵናኑኒ፡ ለትውልደ ትውልድ!”***

*ማለትም፡* ***“መንግሥቱ፡ የዘለዓለም ናት፤ ንግሥናውም፡ ከትውልድ፡ ወደትውልድ እየተላለፈ የሚኖር ነው!”*** *በተባለው፡ በሊቀ ካህናቱ ንጉሠ ነገሥት፡ ኢየሱስ ክርስቶስና በቅድስቲቱ እናት ንግሥት፡ በድንግል ማርያም ለምትመራው፡ ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ነውን? ወይስ፡ ለሌላ? ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ሳይኾን፡ ለሌላው መኾኑማ፡ ይኸው፡ በይፋ ተረጋግጦ ይታያል።*

*ለአንድ ግለሰብ፥ ወይም፡ ለአንድ ምእመን፥ ወይም ለአንድ ካህን፥ ወይም፡ ለአንድ ሃይማኖት ድርጅት፥ ወይም፡ ለአንድ ሕዝብ፥ ወይም፡ ለአንድ አገር፡ በአንድ ጊዜ፡ ለኹለት መንግሥታት፥ ለኹለት ጌቶች፥ ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ፡ መገዛት ይቻለዋልን? አይቻለውም።*

*ታድያ! ካልተቻለው፡ ይህን ድርጊት የሚፈጽሙት ኹሉ፡ በማን ላይ እየዘበቱና እየተሣለቁ ይመስላቸዋል? በፍጡር ላይ ሳይኾን፡ በፈጣሪ ላይ መኾኑን ተገንዝበውታልን? በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚፈጸም፡ ይህን የመሰለው ኃጢአት ደግሞ፡ በምድር ኾነ፡ በሰማይ እንደማይሰረይ፡* ***በመለኮታዊው ቃል የታወጀ ሲኾን፡*** *ታላቁን ኃጢአት አወቀው፡ በድፍረት የፈጸሙት፡* ***እነርሱው ራሳቸው፡ ይህን ያዋጅ ቃል የሚያውቁት አይደለምን? አዎን!*** *ያውቁታል።*

*እንግዲያስ፡ ከዚሁ ታላቅ ኃጢአታቸው፡ በጊዜው፡ በንስሓ ሊመለሱ ይገባቸዋል።*

*ምናልባት፡ ይህን እውነታ ያላወቁ ካሉ፡ በዚህ መልእክታችን አማካይነት፡ እነሆ ማሳወቃችን ነውና፡ እናንተም፡ ኪዳናዊያንና ኪዳናዊያት፡ ላላወቁት፡ በየበኩላችሁ እንዲያውቁ ታደርጉ ዘንድ እናሳስባችኋለን።*

\+ \+ \+